# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

## Catering & Tourism Training Institute

*ዜና መጽሔት* *ቅጽ 1 - ቁጥር 1*

**መጋቢት 2011.ዓም**


ይህ የዜና መትሔት በየወሩ በተቋማችን የተከናወኑ አበይት ተግባራት፣ተደራጅተው የሚወጡበት ነው።


**አዘጋጅ**

**የህዝብና ዓለማቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት**

**አድራሻ**

**ስልክ :- 0115308121**

**Po.B: 4350**

**Email:info.CTTIedu.org**

**WWW.Cttiedu.org**

**Face book:Cttiedu.org**


በውስጥ ገጽ


Inside Story 2

Inside Story 2

*የመጀመሪያ* 2

- ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን 2
- የቦሊንግ 3
- ለችግር 3

**ቀጣይ** 4


## የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሙያ ደረጃን ለማሻሻል ውይይት ተደረገ





**ሚያዝያ 07 / 2011 ዓ.ም**

በሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ባለቤትነት እየተሰራ በሚገኘው ሃገር አቀፍ ሆቴልና ቱሪዝም የሙያ ደረጃ ማሻሻያ ሰነዶች ላይ ውይይት ተደረገ።

የሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የሙያ ማሻሻያው በቂ ጥናትና ውይይት ተደርጎበት የዘርፉን ተለዋዋጭነትን ታሳቢ በማድረግ እንደ ሃገር ብቁ በዘርፉ ብቁ ባለሙያ ለማፍራት በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው ብለዋል።

ከዚህ በፊት በነበረው የሙያ ደረጃ ላይ የታጨቁና ድግግሞሽ የበዛባቸው የብቃት አሃዶች መኖራቸውን ገልጸው አሁን እየተዘጋጀው ያለው የሙያ ደረጃ ይህንንና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ እንደሚያስችል ገልጸዋል።የሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ አካዳሚክና ምርምር ዲን አቶ ግሩም ግርማ በበኩላቸው ከዚህ በፊት የተሰራው የሆቴልና ቱሪዝም ስልጠና

## የዳቦ፣ኬክና ጣፋጭ ምግቦች የማታ ሰልጣኞች ስልጠናቸውን አጠናቀቁ



በሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዳቦ፣ኬክና ጣፋጭ ምግቦች ዝግጅት በደረጃ ሶስት በማታ መርሃ-ግብር ሲከታተሉ የነበሩ ሰልጣኞች ስልጠናቸውን አጠናቀቁ።የኢንስቲትዩቱ የምግብና መጠጥ ትምህርት ክፍል ኃላፊ አቶ ስንታየሁ ወርቁ እንደገለጹት ሰልጣኞቹ በሙያ መስኩ አስፈላጊውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ መደረጉን ገልጸው በእለቱ ስልጠናቸውን ያጠናቀቁ ሰልጣኞች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ስልጠናቸውን ያጠናቀቁ ናቸው ብለዋል።

ስልጠናውን ካጠናቀቁት ሰልጣኞች መካከል ሰልጣኝ ሰላማዊት ቱሉ

## ለሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞች የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ





የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ሰዎች በየትኛውም አጋጣሚ የሚደርስባቸው አደጋ የከፋ ጉዳት እንዳያስከትል ወደ ሀኪም ቤት ሂደው ተገቢውን ህክምና እስኪያገኙ ድረስ የሚሰጠ ጊዜያዊ ህክምና ነው።

ስልጠናውን የሰጡት ሲስተር ምኞት አበበ እንደገለጹት የዚህ ስልጠና ዋና ዓላማ ሰዎች የሚያጋጥማቸውን አደጋ ሙያዊ በሆነ መልኩ እርዳታ የሚሰጥ ሰው ላይ ሌላ ችግር ሳያስከትል በሰብዓዊነት የደረሰበትን ሰው መርዳት የመያስችል ነው ብለዋል። አክለውም በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገራት አደጋ የደረሰበትን ሰው መርዳት የተለመደ እና በህግም የተደነገገ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ስልጠና መውሰድ ተገቢ ነው ብለዋል።

የሥልጠናው ተሳታፊዎች በበኩላቸው ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ከዘርፉ ጋር ተዛማጅ የሆነ ህክምና እርዳታ አሰጣጥ ስልጠና የሚሰጥ ቢሆንም የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች የዚህ ስልጠና ተካፋይ መሆናችን በጣም ጠቃሚ ነው ብለዋል።

## የኢንስቲትዩቱ ማህበረሰብ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አከበሩ






**ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ መጋቢት 16/2011 ዓ.ም**

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰልጣኞችና ሰራተኞች 43ኛውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8) "የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንትናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት" በሚል መሪ ቃል በገነት ሆቴል አከበሩ።

በዓሉ በአገራችን ለ43ኛ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ108ኛ ጊዜ የሚከበር ሲሆን በዋነኝነት በሴቶች ላይ ይደርስ የነበረውን ጭቆና ለማስወገድ የተደረገውን ሁለንትናዊ እንቅስቃሴና ውጤት ከመዘከር ባለፈ ሴቶች ከነበረባቸው ጭቆና ተላቀው በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትና የጾታ እኩልነት የሰፈነበት ምቹ ሁኔታን የመፍጠር አላማን ሰንቆ የሚከበር ተላቅ ሁነት ነው።

በዓሉን በንግግር የከፈቱት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የኢንስቲትዩቱ ሴት ሰልጣኞች ለሁለንትናዊ እኩል ተጠቃሚነት እራሳቸውን ማብቃት አለባቸው፣ ለተለያዩ በሽታዎች ከሚዳርጉ ሁኔታዎችም መራቅ አለባቸው ብለዋል።

በበዓል አከባበሩ ላይ በአንጋፋና ተወዳጅ አርትስቶችና ታዋቂ ግለሰቦች በበጎ ፍቃድ የደም ልገሳና የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ቫይረስ ላይ ያተኮረ የልምድና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

ከዚህም ባሻገር አንጋፋና ተወዳጅ አርቲስቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ለሰልጣኞች ምክር ለግሰዋል።

**ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ ያስመዘገበችው እድገት ከዓለም ቀዳሚ ነው ተባለ::**

ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ የጉዞ መዳረሻ ፈጣን እድገት በማስመዝገብ ከዓለም ቀዳሚ መሆኗ ተገለጸ።

የአለም የጉዞና ቱሪዝም ካውንስል እኤአ በ2019 ባወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ ፈጣን እድገት በማስመዝገብ በጉዞ መዳረሻ ከአለም ቀዳሚ ሆናለች።ከአፍሪካ ደግሞ ርዋንዳ እና ኡጋንዳ ይከተሏታል።

የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ያስመዘገበው 48 ነጥብ 6 በመቶ እድገት በአገሪቱ ኢኮኖሚ 9 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ ሲይዝ ለ 2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል። አሁን ላይ ከኢትዮጵያ ሰራተኛ ኃይል 8 በመቶ የሚጠጋው በዘርፉ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል። አመታዊ ትንታኔው የተሰራው አለም ዓቀፉን የኢኮኖሚ ሁኔታና የስራ እድል ፈጠራ ተጽእኖን መሰረት በማድረግ 185 አገሮችን በማካተት መሆኑን ካውንስሉ አስታውቋል።

በጥናቱ መሰረት ዘርፉ ከአለም አጠቃላይ የምርት እድገት 10 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ ሲኖረው 319 ሚሊዮን ሰዎች ቀጥተኛ የስራ እድል አግኝተውበታል።

በዚህም እአአ በ2018 በአለም አቀፍ ደረጃ ከተፈጠረው አጠቃላይ የስራ እድል 10 በመቶ ምጣኔ ይዟል።

የአለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ቢያሳይም የቱሪዝም ዘርፉ እድገት እአአ በ2019 ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሪፖርቱ አሳይቷል።

የአፍሪካ የቱሪዝምና የጉዞ ዘርፍ እአአ በ2018 ከእስያ ፓስፊክ በመቀጠል ፈጣን እድገት ማስመዝገቡን የካውንስሉ ሪፖርት አስፍሯል።

Source: #Ethiopian News Agency

# የቦሊንግ ስፖርት ቤት ተመረቆ ተከፈተ



በአንጋፋው ገነት ሆቴል ውስጥ የሚገኘው የቦሊንግ ስፖርት ማዕከል እድሳት ተደርጎለት ለስፖርት ማዕከልነት እንዲውል የካቲት 30/ 2011 ዓ.ም በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ አቶ ሀብታሙ ሲሳይ እና የሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ተመርቆ ተከፍቷል፡፡

የቦሊንግ ስፖርት በሃገራችን በ1960ዎች የተጀመረ ሲሆን በገነት ሆቴል የሚገኘውን የቦሊንግ ስፖርት ማዕከል ለመጀመሪያ ጊዜ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተመርቆ ስራ የጀመረ ነው፡፡

የቦሊንግ ስፖርት ማዕከሉን የከፈቱት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታው ሀገራችንን በሁሉም መስክ በዓለም አቀፍ መድረክ ተወዳዳሪ ለማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍልን በማሳተፍ ስፖርቱን ህዝባዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት በበኩላቸው የቦሊንግ ስፖርት በገነት ሆቴል ያለውን ታሪካዊ ሂደትና ቀደምትነት ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው በኢንስቲትዩቱ ውስጥ የሚገኙ ሰልጣኞች በአቶ ታሪኩ ተስፋዬ ፕሮጀክት ውስጥ ስልጠና እየተሰጠባቸው በሚገኙ የስፖርት ዘርፎች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጋር እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ማዕከሉ ከመዝናኛነት ባለፈ ሃገርን የሚያስጠሩ ታላላቅ ባለሙያዎች የሚፈሩበት እንደሚሆን ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል፡፡

## ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን ሙያዊ ስልጠና ለመስጠት ፊርማ ስምምነት ተደረገ



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልኛ ኢንስቲትዩት በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ውስጥ የሚገኙ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የተግባር ስልጠና በመስጠት ያለባቸውን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመቅረፍ ከወረዳው የሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች ጽ/ቤት ጋር የስምምነት ፊርማ ተፈራርሟል፡፡ ተቋሙ በእቅዱ ከተገለጹ ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስኮች መካከል በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት መስጠት ዋነኛው ግብ ነው፡፡

ይህንን መሰረት በማድረግ ኢንስትቲዩቱ በያዝነው በጀት ዓመት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤት ጋር በጋራ በመሆን ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የመጀመሪያ ዙር 54 ሴቶችን የተግባር ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል፡፡

በፊርማ ስነስርዓቱ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ተቋማቸው በተሰማራበት ዘርፍ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን በማሰልጠን ችግሮችን በመቅረፍ የማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ፋሲካ ፍቃዱ በበኩላቸው በወረዳው ውስጥ የሚገኙ እና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይም ሴቶችን መለየትና በፍላጎታቸው መሰረት ለስልጠና በመምረጥ፣ስልጠናውን ላጠናቀቁ ባለሙያዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ከማሰልጠኛ ተቋሙ ጋር በቅንጅት በመስራት የስራ ሁኔታን

## የኢንስቲትዩቱ የአንድ ዓመት ጉዞ ተገመገመ

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ መጋቢት 27/ 2011 ዓ.ም የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አመራርና ሰራተኞች “ከመጋቢት እስከ መጋቢት” የተቋሙን የአንድ ዓመት ጉዞ አስመልክቶ መጋቢት 26/2011 ዓ.ም በገነት ሆቴል ው ይ ይ ት አ ካ ሄ ዱ ፡ ፡ በሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አሰቴር ዳዊት ተቋሙን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር በየደረጃዉ የሚገኙ ሠራተኞች የበኩላቸውን ድርሻ በንቃትና በትጋት በጋራ ተባብሮ መስራት አለባቸው ብለዋል፡፡ ለተቋሙ ሠራተኞች “ከመጋቢት እስከ መጋቢት” ባሉት ጊዜያት እንደ ሀገር አቀፍና በተቋም ደረጃ የተመዘገቡ አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮች በቀረበው መነሻ ጽሁፍና የዘጠኝ ወር የቁልፍ ተግባራትና አበይት ተግባራት አፈጻጸም ዙሪያ ው ይ ይ ት ተ ካ ሂ ዷ ል ፡ ፡ ተቋሙ ለ50 ዓመታት በዘርፉ ሰለጠነ የሰው ሀይል የሚያቀርብ ብቸኛ የመንግስት ተቋም ቢሆንም እንደ አድሜው አንጋፋነት አሁን ያለበት ደረጃ አመርቂ ባለመሆኑ መመህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች መሻሻል አለባቸው ያሉት ጉዳዮችን አ ን ኳ ር አ ን ኳ ር ነ ጥ ቦ ች አ ን ስ ቷ ል ፡ ፡ ውይይቱ በተለይ የፋይናንስ አፈጻጸማቸን ከማዕቀፍ ግዥ ጋር በተያያዘ በመጓተቱ ምክንያት የታቀደውን ያህል መሄድ አለመቻሉ የተገለጸ ቢሆንም ቀጣይ ባሉት ጥቂት ጊዜያት የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንደምሰሩ የአስተዳደርና ልማት ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ ተናግረዋል፡፡ የተቋሙ የከፍተኛ ትምህርት ማዕቀፍ ረቂቅ ደምብ ረጅም ሂደት እየወሰደ እንደሆነና በአሁኑ ጊዜም ሚኒስቴር መስሪያቤቱ የተሸሻለ ረቂቅ ደምብ ለሚኒስትሮች ምክርቤት አስገብቶ ክትትል እየተደረገ መሆኑን የአካዳሚክና ምርምር ዲ ን አ ቶ ግ ሩ ም ግ ር ማ ገ ል ጸ ዋ ል ፡ ፡ በማጠቃለያው ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር የቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ገንቢ በመሆናቸው የተሻለ አፈጻጸም ለማምጣት በጋራ እንረባረባለን ብለዋል፡፡

# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት (ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ)

## Catering & Tourism Training Institute CTTI

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንቲትዩት (ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ) ላለፉት 50 ዓመታት በዘርፉ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማቅረብ፣ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማከናወንና የማማከር አገልግሎቶችን በመስጠት ለሃገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዕድገት የላቀ አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኝ ግንባር ቀደም ተቋም ነው፡፡

ተቋሙ በያዝነው ዓመት ከሰኔ አንድ እስከ ሶስት 2011ዓ.ም 50ኛ ዓመቱን በደማቅ ሁኔታ ላማክበር ዘብግጅት ላይ ይገኛል፡፡



የተቋሙን ሃምሰ ዓመታት ጉ ዞ አስመልክቶ ፣ ግጥም ፣መጣጥፍ፣ እና ሌሎች ጽሑፎች ማቅረብ የምትፈልጉ ተማሪዎችና ሰራተኞች ቢሮ ቁጥር 6 መጥታችሁ ማነጋገር ትቻላላችሁ

## በኢንስቲትዩቱ በቀጣይ ስራዎች ዙሪያ ውይይት ተደረገ





**መጋቢት 07/2011 ዓ.ም**

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በቀጣይ ስራዎች ዙሪያ የተቋሙ የስራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች በተገኙበት በቢሾፍቱ ከተማ የሁለት ቀን ውይይት ተደርጓል፡፡
ኢንስቲትዩቱ የላቀ ስልጠና ለመስጠትና ኢንዱስትሪው በሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲመራ ለማድረግ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ለአስር ዓመታት ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ እየተገበረ ይገኛል፡፡ በፍኖተ ካርታው ከተገለጹት ዋና ዋና የእይታ መስኮች መካከል የላቀ ትምህርትና ስልጠና፣የላቀ ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር፣የላቀ ማማከር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ዋና ዋናዎች ሲሆኑ እስከ አሁን ከእቅዱ አንጻር የተሰሩና ያልተሰሩ ስራዎች በመድረኩ ላይ በጥልቀት ተገምግሟል፡፡
ከዚህ በተጨማሪም በተቋሙ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዶችና የበጀት ዓመቱ የስድስት ወራት እቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡
በውይይቱ ወቅት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት እቅድን በጥልቀት በመገምገም በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረን አጋዥ በመሆኑ ሁሉም የስራ ክፍል በውይይቱ ላይ የተሰጠውን ግብዓት በመውሰድ ተግባራዊ እንዲያደረግ አሳስበዋል፡፡